የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 18
ADDIS ABABA 3rd March, 2020

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፮/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.......ገጽ ፲፪ሺ፪፻፳፰

**<u>Content</u>**

PROCLAMATION No. 1166/2019

Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project Ratification Proclamation …………Page 12228

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፮/፪ሺ፲፪

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</u>**

ለደቡብ ብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል አንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ዩ.ኤስ.ዲ ፩፻፸ ሚሊዮን) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፳፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No. 1166/2019

**<u>A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT-IMPORT BANK OF KOREA</u>**

**WHEREAS,** the Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea stipulating that Export-Import Bank of Korea provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of one hundred seventy million United States Dollar (170,000,000 USD) for financing Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project, was signed in Addis Ababa on 22nd Day of April 2019;

**WHEREAS,** the House of people's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 5th Day of November, 2019;

**NOW, THERFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያ ሥርዓት ማስፋፊያ ፕሮጀክት የሚውል ብድር ከኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፷፮/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፩ በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር ETH-4 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን አንድ መቶ ሰባ ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (ዩ.ኤስ.ዲ ፩፻፸ ሚሊዮን) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Export-Import Bank of Korea Loan Agreement for financing Southern Extension of the National Electricity Grid Power Transmission Project Ratification Proclamation No. 1166/2019".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number ETH-4 signed in Addis Ababa on 22nd Day of April 2019 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export-Import Bank of Korea is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of One Hundred Seventy Million United States Dollar (170,000,000 USD) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the Date of its publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 3rd Day of March 2020.**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**